# በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ የሚደረገውን የትግራይ ገዥዎች የዘር ማጥፋት ዘመቻ በህዝባችን ያላሰለሰ ትግል እናኮላሸዋለን!

ከወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት ህዝብ እ/ኢ/አ ከ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም ጀምሮ በዘረኛውና በወራሪው የህወሃት ቡድን ማንነቱን ተነጥቆ፤ፈጽሞ ሊሆን የማይችለውንና ሆኖ የማያውቀውን ትግሪያዊ እንዲሆን ተገዶ፤ የትግሬ ካባ ተጭኖበት፤ በአልጠግብ ባይ የትግሬ ገዥዎች ለም የእርሻ መሬቱን ተነጥቆ፤ ተወልዶ ካደገበት፣ ልጆቹን ወልዶ ካሳደገበት፣በዳረበትና በኳለበት፣ አያት ቅድመ አያቶቹ ካስረከቡት ቀየው በውጴታ ግጴታ እንዲፈናቀል ተደርጎ፤በስመ ሰፋሪ ከአካባቢው ነዋሪ ማህበረሰብ የማይተናነስ "የትግሬ ሰፋሪ ወወራሪ" ህዝብ አይሉት ግብረ-ሃይል በማሰማራት፡-

፩ኛ- የህዝባችንን ማንነት በተቀነባበረና በአለም ላይ እኩይነቱ በታወቀና በተወገዘ፣ በተለይም አንድን ዘር ከፍተኛ ቁጥር ባለው በሌላ ዘር በመተካት በሚካሄደው የዘር ማጥፋት ወንጀል /Ethnic Cleansing/ ሙሉ በሙሉ በህዝባችን ላይ በመተግበር ጎንደሬ/አማራነቱን ለማጥፋት እየተደረገ ያለው ወንጀልና ግፍ ለመከላከል በአሁኑ ሰአት ህዝባችን በአንድነትና በተባበረ ክንድ ፡-

- የቻለና የደረሱ ልጆች ያሉት አካባቢውንና ዘሩን አላሰደፍርም በማለፍ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል ላይ ሲገኝ
- ያልቻለ ደካማ ህጻናትና ሴት ለጆቹን በማንጠልጠል ዘሩን ለማትረፍና ባለው አቅም ሁሉ ማመጹን ለማጠየቅ ወደ ጎንደር ከተማና አካባቢው መላ ቤተሰቡን ይዞ በመሸሽ
- እዲሁም እጅግ ብዙው ወጣትና ጎበዝ አቅሙ በፈቀደው ሁሉ ወራሪውን ሃይል ከየአቅጣጫው በመታገል ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የአካባቢው ተወላጅ ወጣቶች አድራሻቸው በማይታወቁ የወያኔ የተለያዩ ድብቅ እስር ቤቶች ታጉረው የሚገኙ ሲሆን፤ ይህም እኩይ አላማው ከየ አቅጣጫው እየከሸፈበት የሚገኘው የትግሬው ወራሪ ቡድን፤ እነሆ የጎን ውጋት በመሆን የነጻነት ትግሉን ከየአቅጣጫው የሚያቀጣጥለውን በዲያስፖራ የሚገኘውን የአካባቢውን ተወላጅ ለማዳከምና ህብረቱን ለማናጋት አዲስ ስልት ቀይሶ በመንቀሳቀስ ላይ የገኛል።

አዲሱ ስልት አዲስ የሚያደርገው ከዚህ ቀደም ባለመሞከሩ አይደለም።ይልቁንስ፡-

- የአስፈጻሚው ልዑክ በቀጥታ ከትግሬዎቹ ተስፋፊዎች መካከል ከአድዋዊያን አንዱ መሆኑ ፤
- በዲያስፖራ የሚገኘውን የአካባቢውን ተወላጅ ከአያት ቅድመ-አያቱ ጀምሮ ያካበተውን የመካናይዝድ እርሻ ሙያ ልምድና ችሎታ ታሳቢ ያደረገና ለሀገሩ፣ለወገኑና ለመሬቱ ያለውን የፀና ፍቅር ታሳቢ ያደረገ መሆኑ፤
- የአካባቢውን ተወላጅ በስደት ሌት-ከቀን ሰርቶ ያካበተውን ዶላር፣ዩሮና ፓውድ ለመዝረፍ ከመቋመጥ የተነሳ መሆኑ፤
- በዲያስፖራ የሚደረገውን የነጻነት ትግል አጋርነት በሀገር-ቤት እየተካሄደ ከሚገኘው የወገናችን መራራ የነጻነት ትግል ለመነጠል የተደረገ የትግሬ ገዥዎች የተለመደ እኩይ የከፋፍለህ ግዛው ፈሊጥ አካል መሆኑ።

በአጠቃላይ አዲሱ ስልት በዲያስፖራ የሚገኘውን የአካባቢውን ተወላጅ ለማንበርከክና ከዚህ ቀደም በ ነሀሴ ፳፻ ዓ.ም ለሆዳቸው ያደሩ የወያኔ/ህወሃት ካድሬ ወንድሞቻችንን (ባንዳ የአካባቢውን ተወላጆችን) በመላክ ያልተሳካውን ሴራ ለማስፈፀም አካባቢውን ለረዥም ጊዜያት በመቆጣጠር ቆዳውን እንደ እባብ በማለስለስ ወገናችንን ሲረግጥ፣ሲበዘብዝ፣በሰፈራ ስም በወገኖቹ ሲያስወርር፣ታማኝ ካድሬ ገራፊዎችን በአካባቢው በማሰማራት አልምበረከክ ያሉትን ወንድም እህቶቻችንን ሲገርፍ-ሲያስገርፍና የቆመለትን የጌቶቹን እኩይ የዘር ማጥፋት አላማ ሲተገብርና ሲያስፈጽም፤ ህዝባችንን ሲገዛና ሲያስገዛ የነበረውን ታማኝ የትግሬ ወራሪዎች ሹምና ካድሬ ተጋዳላይ ኣይተ ይትባረክ ዘአድዋ ለአይን ህክምና የመጣ በማድረግ የአካባቢው ተወላጆች በብዛት ወደ ምንኖርበት ኦሃዮ/ኮሎምበስ ግዛት በመላክ የእግረ-መንገድ የ"እንወያይ" ጥሪ በማዘጋጀት በውጭ ሀገር በስደት ለምንኖር የአካባቢው ተወላጆች የተዶለተልን ሰይጣናዊው የአሳዳጆቻችን እኩይ መርዝ መሆኑን ተረድተናል።

ይህ አዲሱ የትግሬ ተስፋፊዎች ሴራ ለም የእርሻ መሬት ከገበሬው ህዝባችን ተነጥቆ በገፍ ለሚያግዙት ሰፋሪ፣ በዝርፊያና በንጥቂያ ላቋቋሙት የኢፈርቱ "ሒወት መካናይዝድ" የእርሻ ተቋምና የዘመኑ የትግሬ ቱጃሮች አካባቢያችንን በሃይል ከተቆጣጠሩ ማግስት ጀምሮ መሬታችንን ሲሸነሽኑት፤ በቅርቡ ደግሞ እንዲሁ ከወያኔ ጋር በማሴር በሃገሪቱ ለም መሬቶች ሁሉ እንደፍልፈል እየገባ የኢትዮጵያን ደሃ አርሶአደር ህዝብ የደም እንባ የሚያስለቅሰው የመሃመድ አላሙዲን የእርሻ ተቋም ከመቀራመት "ያተረፈውን?" ብጥስጣሽ መሬት በአሁኑ ጊዜ በውጭ ለሚኖረው የአካባቢው ተወላጅ በመደለያነት በማቅረብ፤ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ከመላው ወገናችን የኢትዮጵያ ህዝብ፤የአማራ ፣የጎንደር ህዝብ ጋር በአንድነትና በጽናት በመቆም በትግሬው ወራሪ ቡድን የተቃጣብንን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመቀልበስ፤ ወገናችንን ለመታደግና ነጻነታችንን ለመጎናጸፍ የምናደርገውን መራራ ትግል ለማኮላሸትና በመካከላችንም መከፋፈልን ለመፍጠር የታለመ መሆኑን በተጨባጭ ደርሰንበታል።

እንደተለመደው ሁሉ አሁንም ቢሆን በወገናቸው ሀዘንና ድህነት ላይ በልፅገው፣ ከፍ ብለውና ደምቀው ለመታየት የሚቋምጡ እጅግ በጣም ጥቂት "የእፍኝት ልጆች" ከመካከላችን እንደማይጠፉና ከወዲሁ ለጌቶቻቸው መላዕክተኛ የእጅ መንሻ የሚሆን የውስኪና የሙክት ጥሎሽ ያገቡና ያለ-አባታቸው ለትግሬ ተላላኪ ሲያሸረግዱ የሚውሉ ደካሞች መንድሞች በመካከላችን እንዳሉ አረጋግጠናል።ምናልባት ከዚህ ቀደም እንዲሁ ተልከው በመጡት የ "ቁራ መላዕክተኞች" ተወናብደው እራሳቸው ለችግርና ለእንግልት፣ በስደት ለፍተውና መከራ አይተው ያከማቹት ሃብትና ንብረት ለብክነት የተዳረጉትን የ"ብልህ መሳይ" የዋህ ወንድሞቻችን ታሪክ እንዲህ ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው፡-

እንደሚታወቀው ማንኝውም ኢትዮጵያዊ ሀገሩን የማልማትና የማሳደግ ጉጉትና በሃገሩ ሰርቶ የማደግ ፍላጎቱ ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል። በተለይም ደግሞ በስደት ለምንኖር ኢትዮጵያውያን ሀገራችን የዜጎቿ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ተከብሮባት ሁላችንም በእኩልነት ያለ አንዳች አድልኦ የምንኖርባት ሰላማዊት ሀገር ሆናልንና እኛም ለወገናችንና ለራሳችን ያለንን መልካም የልማትና የእድገት ራዕይ ተሸክመን የምንኖር ሲሆን፡ ይህም ህልማችን ሁሌም እንደ ጥላችን የሚከተለንና ዘወትር እረፍትና እንቅልፍ የሚነሳን ጉዳይ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል።

ከዚሁ ከእኛ መካከል የነበሩ ወንድሞች በዚህ ቅን አስተሳሰብ ታውረውና ተነድተው በወያኔ አፈ-ጮሌ ካድሬዎች ውትወታ ተወናብደው ያለ የሌለ ሃብታቸውን በማራገፍ የእርሻ ትራክተሮችን በብዛት በመግዛት ሀገር ቤት ለማስገባት ጥረት ያደረጉ ዝንጉ ወንድሞቻችን በስተመጨረሻ ቃል የተገባላቸውን መሬት በመከልከልና በውድ ዋጋ የተገዙ መኪኖቻቸው ሁሉንም የተጠየቁትን ፎርማሊቲዎች አሟልተው ጂቡቲ ወደብ ላይ ከደረሱ በኋላ ወደሃገር እንዳይገቡ በተለያዩ ሰንካላ መሰሪ መክንያቶች በትግራይ ክልላዊ መስተዳድር በኩል ወደ ሀገር የመግቢያ ደብዳቤ በመከልከል ያደረሰባቸውን ከፍተኛ ግፍ፣እንግልትና መከራ ማስታወስ በእኛው በእራሳችን ላይ የተፈፀመ የትግሬዎቹ ገዥዎች የተለመደ ድራማ በመሆኑ ሌላ ተጨማሪ አስረጂ አያሻውም።

እንግዲህ ይህን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብሎ ማስታወስ የግድ ያሰፈለገበት አብይ ምክንያት፤( የወጋ ቢረሳም የተወጋ አይረሳምና ነው ነገሩ)

፩ኛ - መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚረዳው ሁሉ የህወሃት/ወያኔ ቡድን ለብዙ ዘመናት በሃገሩ ናፍቆት በሚናውዘውና በስደት ላይ በሚገኘው ወገናችን ላይ "ሀገራችሁን በነፃነትና በእኩልነት አልሙ" በሚል መፎክር ሽፋን የሚፈፅመውን የተራ ዱሩዬ "አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ" ውስልትና ለማጋለጥ ሲሆን

፪ኛ- በተለይ በአሁኑ ሰአት በተለያዩ "የልማት ትራንስፎርሜሽን" መፎክሮችና በወያኔ አፈ-ጮሌ ካድሬዎች "ጅንጀና" ፈዘውና ደንዝዘው፤ በዘመኑ የ"አስማታዊ" ብልፅግና እንቁልልጭ ህሊናቸውን አናውዘው ፤ለዘመናት በስደት ተንገላትተው ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ለትግራይ ተስፋፊዎችና ገዢዎች በማስረከብ የጠላቶቻችንን እድሜ ለማራዘምና የደሃውን ወገናቸውን ጣርና ሰቃይ ለማብዛት ከወዲሁ እጅ የሰጡትን ወገኖች ከጥፋት ለመታደግና ከታሪክ ተወቃሽነት ለማዳን ጭምር ነው።

በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ሃገራችን ውስጥ፤ በማንኛውም ቦታ የሚገኘው ወገናችን የሚፈፀምበት መከራና ግፍ እጅግ ተጠናክሮ ቀጥሏል።በተለይም በወልቃይት፣በጠገዴና፣በጠለምት ውስጥ ወገናችን በአካባቢው በሚደረጉ ማንኛውም አይነት መንግስታዊና ማህበራው ስብሰባዎች ተሳተፎ እንዳያደርግ በግልፅ በመታገዱ፤ እነዚህም ስብሰባዎች በሚደረጉበት ወቅት (ለማንኛውም ታዛቢ ግልፅ በሆነ ሁኔታ) የትግራይ ሰፋሪዎች(ሀገሬው ባለጊዜና የንጉስ ዘሮች እያለ ያሞካሻቸዋል)በክብር ወደ መሰበሰቢያ ቦታ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ የአካባቢው ተወላጆች ግን ወደ ውስጥ እንዳይገቡና ምክራቸውን እንዳይሰሙባቸው "ቆሻሻ እንደነካ እንጨት" ወደውጭ እንዲጣል ይደረግና ተወልዶ ባደገበት ሃገሩ በላዩላይ በር እየተዘጋበትና ሰፋሪዎቹ መክረውና ዘክረው እስኪጨርሱ ድረስ እነደ አሮጌ ውሻ በዕዳሪ እንዲቆይ እየተደረገ ከዛም ትግሬዎች መክረው ዘክረው የወሰኑት ውሳኔ ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በእርሱም ላይ ተፈፃሚ እየተደረገበት ይገኛል።

ለመሆኑ ክቡር ኣይተ ይትባረክ ዘአድዋ! በአሁኑ ሰአት እኛን ማወያየት ለምን አስፈለገዎ? ምን ቀረኝ ብለውነው እዚህ ድረስ የመጡት?ለምን ከጎናቸሁ ያለውን እናስተዳድረዋለን ብላችሁ ያለፈቃዱ በሃይልና በማናለብኝነት ረግጣችሁ የያዛችሁትን ማህበረሰብ እዛው አያነጋግሩትም ነበር? ያንን ኩሩ ጀግና ህዝብ "ለማስተዳደር" ወ/ሚካኤልና ገ/ሚካኤል ለዘመናት እየተፈራረቃችሁበትና እራሱን ማስተዳደር እንዳይችል ረግጣችሁ የያዛችሁትን ህዝብ ቤተሰቦች ለማነጋገር በመጨነቅዎ ይሆን እንዴ? ታላቁን የአትላንቲክ ውቅያኖስን አቆራርጠውና ብዙ ሺ ማይሎችን ተጉዘው በራችን ድረስ የመጡልን! ወይስ የተለመደው ዶላራችን ናፍቋችሁ?

በዚህ አጋጣሚ ለእርስዎና ለላከዎት የወያኔ ቡድን አንድ ግልፅ አብይ መልእክት ማስተላለፍ እሻለሁ። ይኋውም፡-

እንኳንስ ከእርስዎ፤በሞራልም ሆነ በደረጃ ከማይመጥኑን ፤ምንም ፈይዳ ከሌለዎት የወያኔ ተራ ካድሬ ጋር መወያየትና መምከር ይቅርና ፤በትግራዩ ገዢ ቡድን ፊታውራሪነት በወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ላይ እየተፈፀመ የሚገኘው የዘር ማጥፋት ወንጀል በወያኔ መንግስትም በኩል እልባት ለመስጠት ፍላጎቱም ሆነ ወኔው አለመኖሩን በተጨባጭ መረጃዎች ለማረጋገጥ ችለናል። ይኋውም፡-

“ለም የጎንደርንና የወሎን መሬቶች ልናመጣልህ ነው” በማለትና “የአማራ ገዳይ” ድለቃችሁን እያስደለቃችሁ የጦርነት እሳት ውስጥ የማገዳችሁት የትግራይ ህዝብ እንዳያምፅባችሁና ሁሌም ለሚያባንናችሁ፣ በእርግጥም ነገ ለሚነሳባችሁ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ህዝባዊ አመፅ/ማዕበል መጠለያ ላለማጣት እንደሆነ ይታወቃል። የሚያሳዝነው ግን እናንተ “ታማኝ” ጀሌዎቹ ያላወቃችሁትና ለጌታችሁ ለአቦ መለስ ግን “ጠንቋዮቻቸው” ሹክ ያሏቸውና ከአሁኑ እየተዘጋጁበት ያለው እውነታ ግን የምትመኩበትና የምታጭበረብሩበት የትግራይ ህዝብ የማይቀረው የህዝብ አመፅ አብይ አካል የመሆኑ እውነታ ነው።

**እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል !**

ውድ መላው የኦሃዮ/ ኮሎምቦስና አካባቢው ነዋሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን !

በተለይ ከአሁኑ ሰአት ጀምሮ በተከታታይ በልዩ ልዩ መርሃ-ግብሮች በትግራይ ገዢዎችና ተስፋፊዎች የማወናበጃ ወጥመድ ውስጥ እንድትወድቁ ኢላማ የተደረጋችሁ በኦሃዮ/ኮሎምበስና በሌሎቹም የሰሜን አሜሪካና ካናዳ ግዛቶች፣እንዲሁም በመላው አውሮፓና አውስትራሊያ የምትኖሩ የወልቃይት፣ጠገዴ፣ሰቲት ሁመራና ጠለምት ተወላጆች በሙሉ !

ከዚህ ከተደቀነብን የትግራይ ገዢ ተስፋፊዎችና የዘራፊዎች ቡድን ከፋፋይና እኩይ ወጥመድ እራሳችንና ወገናችንን በንቃት ጠብቀን፤ በወያኔ የዘር ማጥፋት ቀንበር ተይዞ ለሚሰቃየውና ዘርን የማትረፍ የሞት ሽረት ትግል ለሚያደርገው ወገናችንና ህዝባችን እንደከዚህ ቀደሙ በጽናትና በቁርጠኝነት ከጎኑ መቆማችንን ለማረጋገጥና የነፃነት ትግሉ አካል በመሆን የነፃነታችን ችቦ እስኪንቦገቦግ በፅናት በመቆምና በወልቃይት፣ጠገዴና፣ጠለምት ጭቁን ህዝብ ስም የማደርገውን ይህንን ሀገራዊ ጥሪ በመቀበል

፩ኛ- በተለይ በDec.12,2010 ኦሃዮ/ኮሎምበስ ሊደረግ በታቀደው የወያኔ ካድሪ የ“እንወያይ” ጥሪ ሙሉ በሙሉ ባለመሳተፍ/boycott/ ፣

፪ኛ- በDec.12,2010 ኦሃዮ/ኮሎምበስ ሊደረግ በታቀደው የወያኔ ካድሪ የ“እንወያይ” ጥሪ ሊገኙ የሚዘጋጁ ወንድሞቻችን ተገቢውን ምክርና ወገናዊ ግሳፄ በመስጠት በስብሰባው ላይ ባለመገኘት ፣ እነዲሁም ይህንን ወገናዊ ጥሪ ረግጠው በአሳዳጆቻችን መድረኮች የሚታደሙትን ወገኖቻችንን ለይቶ በማወቅ፣

፫ኛ- በመላው አለም የምትገኙ የአካባቢው ተወላጆችና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ተመሳሳይ ወጥመዶች እንደተዘጋጁላችሁ እንረዳለንና ከወዲሁ ሊደረጉ የታቀዱ ማንኛውንም አይነት ተመሳሳይ የትግራይ ገዢዎችና ተስፋፊዎችን እንደ ፋሽን በልማት ስም የያዙትን የ“እንወያይ” መርዛማና ከፋፋይ መድረኮችን በማኮላሸት፣

በመከራ አለንጋ ለሚገረፈው፤በፍትህ፣በነፃነትና በዲሞክራሲ እጦት ለሚሰቃየውና በትውልድ ቀየው እንደ “ተጠላ ውሻ” በላዩ ላይ ከውጭ በር ለሚዘጋበት ወገናችን ያለንን ፍቅር፣ክብር፣ተቆርቋሪነትና የትግል አጋርነት በድጋሚ እንድናረጋግጥ ጥሪየን አስተላልፋለሁ።

**ለወልቃይት፣ጠገዴ፣ጠለምትና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ መብቶች መከበር የምናደርገው ትግል በህዝባችን የተቀናጀ መስዋዕትነት ግቡን ይመታል !**

**የወልቃይት፣ጠገዴና፣ጠለምት ህዝብ ትላንትም፤ዛሬም፤ነገም ጎንደሬ አማራነቱን ማንም ፈፅሞ ሊለውጠው አይቻለውም !**

**ሎጋው ዘጫቆ**

**ህዳር 29, 2003 ዓ.ም**

**ኦሃዮ/ ኮሎምበስ**